## ትምህርት 9

### የጌታ መንፈስ ቅዱስ ማንነት መረዳት፡-

እንደ እግዚአብሔር አብና ወልድ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ሙሉ መለኮታዊ ማንነት ያለውና በትምህርት 8 የተዘረዘረው የእግዚአብሔር ባህርይ ሁሉ የእርሱም ባህርይ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አገልግሎቱን ፈጽሞ ከሄደ በኂላ መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም እንደ ሚመጣ/እንደ ሚልክልን ተናግሮ ነበር። እግዚአብሔር አብም መንፈስ ቅዱስን እንደሚመጣ የተስፋ ቃል ሰጥቶ ነበር። በዚሁ መሰረት በሃዋሪያት ዘመን በበዓለ ሃምሳ ቀን (ኦን ዘ ዴይ ኦፍ ፔንታኮስት) መንፈስ ቅዱስ በጌታ ሐዋሪያት ላይ መጣና ይጸልዩ በነበረበት ስፍራ በሁሉም ላይ ሞላባቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው እግዚአብሔር በሰጠው ቃሉ መሰረት ለመኖር ጥረት በሚያደርጉ፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም እንደመጣና በስራ ላይ እንዳለ በሚያምኑት ሁሉ፣ አሁንም ሆነ ወደ ፊት ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ እስከ ሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሊሰራ የመጣበትን የወንጌል ማስፋትና ማጽናት ሥራ ያከናውናል።

**ጌታ መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጣቸው አገልግሎች ዋና ዋናዎቹን ከዚህ በታች ሰፍረዋል፡-**

1. የአግዚአብሔርን ቃል ለሰው ልብ ያበራል/መረዳት ይሰጣል (Revelation and Inspiration of Scripture) ዮሐ 16፡14-15፣ 14፡26፣ 1ቆሮ 2፡13፣ 2ጢሞ 3፡16-17)
2. በጌታ ኢየሱስ በእውነት ላመኑት ከመንፈስ ቅዱስ እንዲወለዱ በማድረግ ቀድሞ በኃጢአት ምክንያት በሞተው መንፈሳቸው ምትክ አዲስ መንፈስ በውስጣቸው ስለሚያኖር ዳግመኛ የተወለዱ ያደርጋቸዋል (Regenerating Believers) ዮሐ 3፡5-7
3. በጌታ ያመኑትን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃል (Baptizing of Believers፣) ሮሜ 6፡3-5፣ ገላ 3፡27-28) ይሄ ከውኃ ጥምቀት የተለየ ሲሆን በየትኛውም የዓለም ክፍል ያሉ በጌታ ኢየሱስ ያመኑ ሁሉ የወይኑ ግንድ ከሆነው ከጌታ ኢየሱስና እርስ በራሳቸው የአንድ አካል ክፍል የሚሆኑበት ነው። ይሄ የሚሆነው በጌታ ኢየሱስ ባመኑበት በዚያው ቅጽበት ነው።
4. በጌታ ኢየሱስ ያመኑትን የዳኑ መሆናቸውን ያትማል (Sealing of Believers፣) ይሄ ማህተም በጌታ የመዳኛችንና የዘላለም ሕይወት ወራሾች መደረጋችን ማረጋገጫ ነው። የሚከናወነውም ንስሃ ገብተን ጌታን በተቀበልንበት ጊዜ ነው። ኤፌ 4፡30 ከተራ ቁጥር 2 እስከ 4 የተጠቀሱት በአንድ አማኝ ውስጥ የሚከናወኑት አንዴ ብቻ ነው እንጂ አይደጋገሙም፡ ፡
5. አማኞችን መሙላት (Being Filled by The Holy Spirit); ጌታ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን አማኝ የሚሞላው፣ ጌታ ኢየሱስን ባመነበት ጊዜ ወዲያውኑ ወይም ቆየት ብሎ ሊሆን ይችላል። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በአንዴ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን በየጊዜው የሚደጋገም ነው። ኤፌ 5፡18

6. በጌታ ኢየሱስ ጌትነትና አዳኝነት ባመነ ማንኛውም አማኝ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ይኖርበታል። መንፈስ ቅዱስ በአማኜ ውስጥ ቢኖርም በመንፈስ ቅዱስ ሳይሞላ ቆየት ሊል ይችላል። (Indwelling of Believers) 1ቆሮ 3፡16
7. ስለ አማኞች የተለያየ ጉዳይ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይማልዳል (Interceding for Believers) ሮሜ 8፡26
8. የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ሆነው እውነት ሁሉ ይመራል። (Guiding Believers) ዮሐ 16፡13
9. አማኞች ክፉ ስራን እያስወገዱ መልካም ፍሬ እያፈሩ እንዲሄዱ ያግዛል። (Helps in producing Fruit) ገላ 5፡22-23
10. ልዩ ልዩ የአገልግሎት ስጦታዎችን (የሐዋሪያነት፣ የነብይነት፣ የአስተማሪነት፣ የወንጌላዊነት፣...ወዘተ) ይሰጣል። በጌታ ኢየሱስ ላመኑት ነው የተለያየ የአገልግሎት ስጦታ የሚሰጠው። ኤፌ 4፡11
11. የአመጽ መንፈስ ስራ አሁን ካለው እጅግ በከፋ ሁኔታ እንዳይገለጥ ይከለክላል፣ (Restricts the power of lawlessness) 2ተሰ 2፡6-7

*መንፈስ ቅዱስ በመድኃኒታችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን አማኞችንና አጠቃላይ ቤተ-ክርስቲያን የኃይልና የድል ሕይወት መኖር የሚያስችል፣ በደረስንበት በየትኛውም ስፍራ አብሮን የሚሆን፣ የሚያነቃቃን፣ የሚናገረን፣ የሚዳስሰን፣ ብቻችንን እንዳልሆንን በማሳወቅ የሚያበረታታን ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላ ክርስቲያን የአግዚአብሔር ፍቅር፣ ታላቅ መልካምነትና የወንጌሉ ቃል እውነት በተግባር በሕይወቱ ማየት ስለማይችል በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ራስን ዝግጁ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ፣ ክርስትና ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ የፍቅር ዝምድና ግንኙነት እንደሆነ እንዲያውቅ የሚያደርገው፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ በሚያፈሰው ቀድሞ ፈጽሞ አይቶት በማያውቀው ፍቅር፣ ሰላምና ደስታ ነው፡፡*

### *መንፈስ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመሞላት የሚያስፈልግ ዝግጅት፡-*

1. *ሐሥ* 2፡37-39፣ *በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሲህነት/አዳኝነት አምኖ፣ ኃጢአትን ተናዝዞ፣ ንስሃ ገብቶ፣ የውሃ ጥምቀት ትምህርት ወስዶ መጠመቅ ነው (አንዳንድ ጊዜ ግን ገና ለመጀመሪያ ጊዜ የወንጌሉን ቃል በመስማት ላይ እንዳሉ ብቻ ሊሞላባቸው ይችላል)፡፡ ይህን ካደረጉ በኋላ ሃጢአትን ከመደጋገም ተቆጥቦ፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል በመኖር መልካም ግንኙነትን ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ለመመስረት መጠማት ያስፈልጋል፡፡ ቀድሞ ይኖሩበት ከነበረ በኃጢአት የተበከለ አኗኗር በመጸጸትና ንስሃ በመግባት የኃጢአት ስርየት ከተቀበሉ በኋላ ከእንግዲህ ከእግዚአብሔር እንደ ተማሩት፣ መንፈስ ቅዱስም እንደ ሰጠው ምሪት ለመኖር ፈቃደኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡*

2. *ሐሥ* 8፡14-17፣ 19፡1-7፣ *መለኮታዊ ማንነት ያለው ሶስተኛው አካል ጌታ መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም መጥቶ አጠገባችን ያለ መሆኑን ማወቅ /እውቅና መስጠት፡፡*

በሃዋሪያት ዘመን ይሰራ እንደ ነበረው አሁንም በመስራት ላይ እንዳለ አምኖ በእርሱ ለመሞላትና ለመመራት መፈለግ/ፈቃደኛ መሆን ብቻ ሳይሆን መጠማት ይገባል፡፡ አንዳንድ ቤተ እምነቶች መንፈስ ቅዱስ አሁን በዓለም ውስጥ እንዳለና በስራ ላይ መሆኑን የማይቀበሉ ስለሆኑ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ እንዳይሰራ ይገድቡታል፡፡ እርሱ ጨዋ ስለሆነ ያማያምኑትን አስገድዶ በእናንተ እሰራለሁ አይልም፡፡

ሁለተኛው ጥማት በጽድቅ ሕይወት ለመኖር በውዴታ/ሆን ብሎ የጽድቅ ሕይወት መጠማትና መለማመድ ሊሆን ይገባል፡፡ ሐሥ 19፡2-6

**ጌታ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ወደ ዓለም ልኮልን በመምጣቱ፣ በዓለም ውስጥ ማለትም በአጠገባችን ያለ መሆኑን መረዳት፡፡** ሐሥ 19፡1-7 በጌታ ኢየሱስ አምነው ተጠምቀው የነበሩ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ መኖርን በማስተዋወቅ ሲጸለይላቸው የተሞሉ አሉ፡፡ ሐሥ 1፡4-5፣ 2፡1-4

በበዓለ ሃምሳ ዕለት እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ ቃል መሰረት መንፈስ ቅዱስን ወደ ዓለም ስለ ላከልን ከዚያ ቀን ጀምሮ ጌታ ኢየሱስን በእምነት የተቀበሉ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ ያሉ ስለሆነ ያልተሞሉትንም በማንኛውም ፈቃዱ በሆነና እነርሱም ልባቸውን ለእርሱ ከፍተው ባገኛቸው ጊዜ ሊሞላቸው ይችላል፡፡

3. በጌታ ያመነ ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዲሞላ ሊጸለይለት የሚያስፈልግ መሆኑን፡- ሐ/ሥ 8፡14-17 አንዳንዴ በጌታ ያመኑት፣ ማንም አገልጋይ ሳይጸልይላቸው በጉባኤው መካከል መንፈስ ቅዱስ የሚሞሉበት ጊዜ አለ፡፡ በጌታ ኢየሱስ አምነውና ተጠምቀው የነበሩት መንፈስ ቅዱስ ሳይሞሉ ከቆዩ፣ ብዙውን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በተሞሉ አማኞች እጅ ተጭኖ ወይም እጅ ሳይጭኑም ሲጸለይላቸው ይሞላሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሐር ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስን የሚሞላው እጅ ጭኖ የሚጸልየው አገልጋይ አለመሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሐሥ 8፡18-20፡፡ እያንዳንዱን አማኝ መንፈስ ቅዱስን ለራሱ የሚሞላው/የሚቀበለው ከእግዚአብሔር ነው፡፡ የሚጸልየው አገልጋይ እጅ ሳይጭን ቢጸልይም የተጸለየለቱ አማኝ መንፈስ ቅዱስ ሊሞላ ይችላል፡፡

ሐሥ 10፡44፡45፣ ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር የሚያየው ግን ልብን ነው፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ያላቸው ሰዎች እርሱን ይበልጥ ለማወቅ በመጠማት ለመጀመሪያ ቀን ቃሉን በመስማት ላይ እንዳሉ የውሃ ጥምቀት ሳይጠመቁና ሳይጸለይላቸው ቃሉ እየተሰበከ እያለ መንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አሉ፡፡

4. ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የሚሞሉ አማኞች አብዛኞቹ በልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ ስለ ሚሰጣቸው በአዲስ ልሳን/ቋንቋ እንዲናገሩ ከውስጣቸው ገፍቶ የመጣ ከሆነ በልሳን መናገር፣ ተናጋሪውን የሚያንጽ ኃይል ስላለው አፍነው በመያዝ ፈንታ መናገር ይገባቸዋል፡፡

5. እንዳንድ በዚህ ልምምድ ውስጥ ያላለፉ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እየተከናወነ ያለ እውነት ስለ ማይመስላቸው፣ የሚያጥላሉና የሚነቅፉ ብቻ ሳይሆን የሃሰት/የማስመሰል ስራ ነው፣ ወይም አጋንንታዊ ነው ብለው የሚያንቋሽሹት ወሬ ስላለ አንተም/አንቺም እንደዚህ ሲናገሩ ሰምተህ/ሽ ከሆነ ሰው ሰራሽ ወሬ ስለሆነ አምኖ መቀበል አይገባም፡፡
6. አንተም መንፈስ ቅዱስ ስትሞላ ልሳን እንድትናገር ከውስጥህ ካነሳሳህ እንቢ ብለህ በማዳፈን/ድምጽ እንዳታወጣ በማፈን ፈንታ ማንንም ሳትፈራና ሳታፍር የመጣልህን ልሳን በመናገር ማውጣት አለብህ፡፡ ከውስጥ ገፋፍቶ ሳይመጣ፣ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና የተገፋፋ አስመስሎ ቢናገር ሃጢአት ነውና እንደዚያ ላለማስመሰል መጠንቀቅ ይገባል፡፡

አዳዲስ አማኞች መንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ከሚጸልየው አገልጋይ በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች ለሚጸለይለቱ ሰው ተጠግተው/ቀርበው መንፈስ ቅዱስ ሲሞላ የሚወድቅ ከሆነ ለመደገፍ ሊገኙ ስለሚችል ተገልጋዩን የተለያየ የሚያምታታው ነገር እንዲያደርግ ሳይናገሩ ሊወድቅ ሲል ብቻ፣ ድምጽ ሳያሰሙ ለመደገፍ ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡

## አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱን እንዴት ያውቃል?

በመንፈስ ቅዱስ በሚሞሉበት ወቅት የሚሆኑት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. አብዛኛውን ጊዜ ሁኔታው የሚፈጸመው በድንገት ነው፡፡ አሁን መንፈስ ቅዱስ ትሞላለህ ተብሎ ሳይነገር፣ ወይም ሌላ ምልክት ሳያዩ አማኞች ለአምልኮ በተሰባሰቡበት ጉባኤ፣ ወይም በግል ቤት ውስጥ እየጸለዩ፣ የእግዚአብሔር ቃል እያነበቡ ሳሉ፣ ከየት መጣ ሳይባል ድንገት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለት ሰዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው ቆመው እየጸለዩ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ አንዱን ሰው ብቻ ለይቶ ሊሞላው ይችላል፡፡

2. መንፈስ ቅዱስ በሚሞሉበት ወቅት አደርጋቸዋለሁ ተብለው በጭራሽ ታስበው ወይም ታቅደው ያልበነሩ ክስተቶች መታየት፤ ለምሳሌ፡- ከፍ ባለ ድምጽ መናገር፣ መሳቅ፤ መጮህ ይከሰታል፣ (የሚናገሩት ነገር በማያውቁት አዲስ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፡፡)

3. የተለያየ የሰውነት እንቅስቃሴ ማሳየት (የሰውነት በኃይል መርገፍገፍ/መንቀጥቀጥ፣ ወደላይ መዝለል፣ መቆም ተስኖ ወለሉ ላይ ለተወሰነ ጊዜ መውደቅና መነሳት አለመቻል…) ያጋጥማል፡፡

4. የሚሰሙ የተለያዩ ስሜቶች (አይተውት የማያውቁት ታላቅ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ የእንባ መፍሰስ … ወዘተ) መንፈስ ቅዱስ በተሞላው ሰው ይታያሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ የሚሰማው ስሜት የሚያውክ ወይም የሚያስጨንቅ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የሰላም መንፈስ ነው እንጂ የሁከት መንፈስ አይደለም፡፡

5. ሁለንተና በመንፈስ ቅዱስ መወረር፤ ሐ/ሥ 9፡4-8፣ ራዕ 1፡17፤

6. መለኮታዊ ኃይል በመላ ሰውነት ውስጥ እያለፈ መሆኑን ይታወቃል፤
7. የሚያምኑ ሰዎች አጠገብ ካሉ በሁኔታው ይገረማሉ፣ እግዚአብሔርንን ያመሰግናሉ፣ የማያምኑ ሰዎች ካሉ ግን ስለ ማያውቁት የሚያፌዙ ሊያጋጥሙ ይችላል፡፡

መንፈስ ቅዱስ መሙላቱን ካበቃ በኋላ እነዚህ ከላይ ከ1-5 የተዘረዘሩ ነገሮችም ያበቃሉ እንጂ ለረጅም ሰዓታት አይቀጥሉም፡፡ በሌላ ቀን መልሶ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እየሆነ ይደጋገማል፡፡ ኃጢአት በማድረግ ጸንተው ከቀጠሉ ግን መንፈስ ቅዱስ ስለሚያዝን ሊቋረጥ ይችላል፡፡

© ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.